# የዓለም ኤድስ ቀን

## “ኤችአይቪን ለመግታት፣ ዓለምአቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላፊነት”

የፌዴራል ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያ
እና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# 1.መግቢያ

ኤችአይቪ መከሰቱ ከታወቀበት እኤአ ከ1981 ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ32.7 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን በኤድስ ምክንያት ያጡ ሲሆን 38 ሚሊዮን ሰዎች ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ኤችአይቪ በደማቸው እንደሚገኝ ይገመታል፡፡ በየዓመቱ 1.7 ሚሊዮን የሚሆኑ አዲስ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎች እንዳሉና 690,000 ሰዎች ለህልፈት እንደሚዳረጉ መረጃዎች ያሳያሉ (UNAIDS FACT SHEET 2019)፡፡

የሀገራችን የኤችአይቪ የስርጭት ምጣኔ 0.93% ሲሆን በዚህም ስሌት 669,236 የሚሆኑ ወገኖች ኤችአይቪ በደማቸው እንደሚገኝ ሀገራዊ የኤችአይቪ ስርጭት ግምት (HIV ESTIMATES AND PROJECTION SPECTRUM, 2019) ያሳያል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 413,547 (61.8%) ያህሉ ሴቶች ናቸው፡፡ ሆኖም የስርጭቱ ምጣኔ ከክልል ክልል፣ ከአንድ ቦታ ሌላ ቦታ፣ በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሁም በከተማና በገጠር በከፍተኛ ደረጃ የሚለያይና አዳዲስ በኤችአይቪ የመያዝ ምጣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚፈለገው መጠን እየቀነሰ እንዳልሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

እ.ኤ.አ በ2019 በሀገራችን 14,843 ሰዎች አዲስ በኤችአይቪ የተያዙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ ማለትም 67% የሚሆነው አዲስ የሚያዙ ሰዎች ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች የሚገኙ አምራችና የነገ የሀገር ተረካቢ የሆኑ ህጻናት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ 20% አዳዲስ የተያዙ ሰዎች ዕድሜያቸው ከ20-24 ዓመት የሚሆኑ ወጣቶችና 19% የሚሆኑት ደግሞ ከ0-4 ዓመት የሚገኙ ህጻናት ናቸው፡፡



በኤች አይቪ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መደገፍና መንከባከብ የሁላችንም ኃላፊነት ነው!

በአሁኑ ወቅት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የዓለምን ትኩረት በእጅጉ የወሰደበት ጊዜ ላይ የምንገኝ ሲሆን፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በማህበረሰቡ ላይ እያስከተለ ያለውን ሁለንተናዊ ጫና ለመቀልበስ የሚደረገው ጥረት የኤችአይቪ ወረርሽኝ ቁጥጥር እና ኤድስ የህብረተሰቡ የጤና ችግር ወደ ማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ የተቀመጠውን ግብ ስኬት ይወስነዋል፡፡ የተባበሩት መንግስታት የኤድስ ፕሮግራም (UNAIDS) ወቅታዊ መግለጫ እንደሚያሳየው ጥምር የሆነው የኤችአይቪና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሊገታ የሚችለው መድሎና መገለልን በመቀነስ፡ የሰው ልጆችን ማዕከል ያደረጉ ስልቶችን በመቀየስና ሰብዓዊ መብቶችንና የሥርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን መሰረት ያደረጉ ሁለንተናዊ ምላሾችን መስጠት ሲቻል መሆኑን ያስረዳል፡፡

የኤችአይቪ/ኤድስ ወረርሽኝን መግታት በበሽታው ምክንያት ሕይወታቸውን ላጡ 32.7 ሚሊዮን የሚገመት ቁጥር ላላቸው የዓለም ሕዝቦች ሲባል ከታሪካዊ ግዴታነትም በላይ ሲሆን፤ ለቀጣዩ ትውልድ በጤናው ረገድ ይበልጥ ምቹ፣ እኩልነት የተረጋገጠ ባትና ፍትኃዊነት የሰፈነባት ዓለም ለማስረከብ መሰረት እንደ መጣያ ጥሩ አጋጣሚ ተደርጎ ሊወሰድም ይችላል፡፡ የኤድስ ወረርሽኝን ማቆም መቻል ለሌሎች የጤናና የልማት ጥረቶች መነቃቃትን ከመፍጠር ባሻገር በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ሥራዎችን በዘርፈ-ብዙ አጋርነት መርህ በአንድ ላይ ሆነን በትብብር መስራት ከቻልን ማሳካት የማ ንችለው ምንም ነገር እንደሌለ ማሳያ የሚሆን ነው፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስ ገባት የዘንድሮው የዓለም ኤድስ ቀን “ኤችአይቪን ለመግታት፣ ዓለምአቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላፊነት” በሚል መሪ ቃል ህዳር 22 ቀን 2013 ዓ.ም በድምቀት ተከብሮ የሚውል ሲሆን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት መሆኑ በዓሉን ልዩ ያደርገዋል፡፡

## 2. የ2013 ዓ.ም የሚከበረው የዓለም ኤድስ ቀን የመሪ ቃሉ ፅንሰ ሀሳብ

### “ኤችአይቪን ለመግታት፣ ዓለምአቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላፊነት”

በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ኤችአይቪ በደማቸው ለሚገኝባቸውና በቫይረሱ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ድጋፋቸውን ለማሳየት እንዲሁም በኤድስ ህይወታቸውን ያጡትን ወገኖች ለማስታወስ በየዓመቱ ህዳር 22 ቀን የዓለም ኤድስ ቀንን ተከብሮ ይውላል፡፡

እ.ኤ.አ በ2020 የዓለም ትኩረት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በጤና፣ በህይወትና በኑሮ እያስከተለው ባለው ተጽዕኖ ላይ አርፏል፡፡ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጤና ከሌሎች ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች ለምሳሌ፡- እኩልነት ከማስፈን፣ ከሰብአዊ መብቶች፣ ከፆታ እኩልነት፣ ከማህበራዊ ጥበቃና ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር እንዴት ጠንካራ ቁርኝት እንዳለው አሳይቶናል፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ዓመት የዓለም ኤድስ ቀን “ኤችአይቪን ለመግታት፣ ዓለም አቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላፊነት” በሚል መሪ ቃል ይከበራል፡፡



ራሴን እና ቤተሰቤን ከኤችአይቪና ከኮሮና ቫይረስ ለመከላከል ተገቢውን ጥንቃቄ አደርጋለሁ፡፡

በወረርሽኝ ወቅት ሁሉም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ እስኪሆን ድረስ ማንም ደህንነቱ የተጠበቀ እንደማይሆን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመታዘብ የቻልን ሲሆን ስኬታማ ምላሽ ለመስጠት ተጋላጭ ሰዎችን ወደኋላ መተው አማራጭ ሊሆን አይችልም፡፡ አድሎና መገለልን ማስወገድ፣ ሰዎችን ማዕከል ማድረግ፣ ሰብዓዊ መብቶችንና ጾታን መሰረት ያደረጉ ስልቶችን መጠቀም የኤችአይቪ እና የኮቪድ-19 ጥምር ወረርሽኞችን ለመግታት ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው፡፡

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በህብረተሰባችን ውስጥ የሚገኙ ስር የሰደዱ ልዩነቶች ጎልተው እንዲታዩ አድርጓል፡፡ ይህ ወረርሽኝ እንደ ሌሎቹ የጤና ቀውሶች ሁሉ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን እና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳ ይገኛል፡፡ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፤ ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች፣ ሴቶችና ልጃገረዶች፣ ይበልጥ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች የነበሩባቸውን ችግሮች ይበልጥ እንዲባባስ ያደረገ ሲሆን መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች ተደራሽ ያለመሆን፣ ለኤችአይቪ ተጋላጭ የሆኑና መገለል የሚደርስባቸው ወገኖች ተጋላጭነት የሚያባብስ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች መስፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህንን ተግዳሮት ወደ ጥሩ አጋጣሚ በመቀየር ነገሮችን ከወትሮ በተለየ መልኩ በትብብር ለማከናወን እንደ ማንቂያ ደወል ይሆናል፡፡ ኤድስን የማህበረሰብ ጤና

ስጋት ወደማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ የተያዘው ግብ ስኬት ለኮቪድ-19 በሚሰጠው ምላሽ ላይ የተመሠረተ ነው።

የአመራሩና የማህበረሠቡ ተሳትፎ ለኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ ስኬት የማይተካ ሚና እንደነበረው ሁሉ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን በመግታቱ ረገድም ቁልፍ ሚና ይኖረዋል። የማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎና ለጋራ ዓላማ በትብብር በኤችአይቪ/ኤድስ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች መረጃ፣ አገልግሎት፣ ማህበራዊ ጥበቃ እንዲሁም ተስፋ በመስጠቱ ረገድ ከፍተኛ አሰተዋፅዖ እንዳበረከተ ብዙ ተሞክሮዎችን አይተናል። ይሁን እንጂ ለጋራ ዓላማ መተባበር የማህበረሰቡ ኃላፊነት ብቻ ሊሆን አይገባም። መንግስታዊ ተቋማት፣ ለጋሽ ድርጅቶች፣ የሐይማኖት መሪዎች፣ ሲቪክ ማህበራትና እያንዳንዱ ግለሰብ የኤችአይቪ ስርጭት በመግታት ጤናማና ለመኖር ምቹ የሆነች ሀገር በመገንባት ሂደቱ የማይተካ አሻራቸውን ማሳረፍ ይጠበቅባቸዋል።

የኤች አይቪና የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል በአንድነት እንቁም!

የፖለቲካ ቁርጠኝነት ምን ያህል ለውጥ ሊፈጥር እንደሚችል በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የታየ ሲሆን መንግስታት ያስቀመጧቸው አዳዲስ ጠንካራ የፖሊሲ እርምጃዎችና ፈሰስ ያደረጉት መዋዕለ-ነዋይ የብዙዎችን ሕይወት ሊታድግ ችሏል። በሀገራችን ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ የፀረ- ኤችአይቪ/ኤድስ ህክምና እንዳይቋረጥ የተደረገውን ሀገራዊ ጥሪ ተከትሎ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት መካከል ከፍተኛ ትብብር ያስተዋልን ሲሆን የጤና ባለሙያዎችም ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል። እ.ኤ.አ በ2030 ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር የማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ በተያዘው ዕቅድ የመጨረሻዎቹ አስር ዓመታት ላይ እንደመገኘታችን መጠን ከግቡ ለመድረስ ከዚህ በፊት ውጤት ያስመዘገብንበትን የአመራር ቁርጠኝነት መልሰን ማረጋገጥ ተተኪ የሌለው መፍትሄ ነው።

# 3. በሀገራችን የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ የተመዘገቡ ውጤቶችና እያጋጠ ሙ ያሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች

## 3.1 የተመዘገቡ ዉጤቶች

ሀገራችን የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ ወረርሽኙ በማህበረሰቡ ጤናና በሰብ አዊ ደህንነት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በማቃለል ረገድ ከፍተኛ ውጤት አስመዝ ግቧለች። ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ በፌደራል ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት ፣ በጤና ሚኒስቴር እና በልማት አጋሮች  በጋራ በተደረጉ ጥረቶች፡-

- በየዓመቱ አዲስ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት በ46 በመቶ እና በኤድስ ምክንያት የሚከሰትን ሞት በ52 በመቶ በላይ እንዲቀንስ ተደርጓል (FHAPCO, 2019)።

- የኤችአይቪ ስርጭት ምጣኔ በ1990ዎቹ መጨረሻ ከነበረበት 3 በመቶ  በ2017 ወደ 1 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል (FHAPCO,  2019)።

- ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔ (በ6 ሳምንታት ውስጥ እና የጡት ማጥባት ጊዜን ጨምሮ) እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት 16% እና 30.2% እ.ኤ.አ በ2019 ወደ 8.9% እና 16.9% በተከታታይ በመውረድ ሁለቱም በ44 በመቶ እንዲቀንስ ተደርጓል (FHAPCO, 2019)።



ኤች.አይ.ቪ በደሜ ይገኛል፤ ቤተሰቦቼ የኤች.አይ.ቪ ምርመራ እንዲያደርጉ ኃላፊነ ቴን እወጣለሁ!

- በ2019 የኤችአይቪ በደማቸው ይገኛል ተብሎ ከሚገመቱ ወገኖች መካከል 79 በመቶ የሚሆኑት ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁና ከእነዚህ መካከል 90 በመቶ ያህሉን ደግሞ የፀረ-ኤችአይቪ መድሀ ኒት ላይ እንዲቀመጡና መድኃኒት ከሚወስዱት ውስጥ 91 በመቶ ያህሉን የቫይ ረስ ልኬት መጠን በሚፈለገው መጠን እንዲወርድ ማድረግ ተችሏል (MOH እና FHAPCO, 2019)።

## 3.2 ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የተገኘውን ውጤት ለማስቀጠልና በ2030 ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር ወደማ ይሆንበት ደረጃ ለማድረስ የተያዘውን ሀገራዊ ራዕይ ዕውን ለማድረግ መፍትሄ የሚ ያስፈልጋቸው ተግዳሮቶች አሉ፡፡ ተግዳሮቶቹ እርስ በርስ የተሳሰሩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ከዚህ ቀደም ብሎ ለተመዘገበው የዘርፈ-ብዙ ምላሹ ስኬት ከፍተኛ ሚና የነበረው የአመራሩ ቁርጠኝነት ዛሬ ላይ መታየት አለመቻል ዋናነኛው ተግዳሮት ሲሆን ማሳ ያዎቹም የአመራር አደረጃጀቶች (ኤድስ ምክር ቤት ፣ የሥራ አመራር ቦርድ በሚፈ ለገው መልኩ አለመቋቋምና አለመጠናከር)፣ ተቋማት የኤችአይቪ/ ኤድስ ሜይን ስትሪሚንግ ፕሮግራሞችን በባለቤትነት አለመተግበር ከችግሩ አስቸኳይነትና አሳ ሳቢነት አንፃር ጉዳዩ የሚፈልገውን የሰውና የገንዘብ ኃይል በወቅቱ የማግኘት ተግ ዳሮት በዘርፈ-ብዙ ምላሹ ላይ እያጋጠሙ ካሉት ተግዳሮቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

- ይበልጥ ተጋላጭና ቅድሚያ የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮሩ እንደ የማ ህበረሰብ ንቅናቄና የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ያሉ የፀረ-ኤችአይቪ መከላከል ፕሮ ግራሞችና አገልግሎቶች አለመጠናከርና የተደራሽነት ዉስንነቶች ኤችአይቪ በደ ማቸው የሚገኝ ወገኖች ራሳቸውን እንዲያውቁና አውቀውም ሕክምናውን እንዲ ጀምሩ ለማድረግ የሚያስችል ፍላጎት ከመፍጠር አንፃር ትልቅ ክፍተት መኖር፡፡

- አዲስ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር በሚፈለገው መጠን መቀነስ ያልተቻለ ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረ በት በ2020 በ75 ከመቶ ለመቀነስ የተቀመጠው ግብ ቢኖርም እስከ እ.ኤ.አ 2019 መጨረሻ ድረስ ማሳካት የተቻለው 46 ከመቶ ብቻ ነው፡፡

አስተዋይ ነኝ፤ ኮንዶምን ሁልጊዜና በትክክል በመጠቀም ራሴን ከኤችአይቪ እከላከላለሁ!

- የኤችአይቪ ምርመራ አገልግሎት በመንግስትና በግል የጤና ተቋማት እንዲሁም ማህበረሰቡ ድረስ በመዝለቅ እየተሰጠ የሚገኝ ቢሆንም አዲስ በኤችአይቪ የሚያዙ ሰዎችን ከማግኘት አንፃር የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ መሆን አልቻ ለም፡፡ በ2010 ዓ.ም 9.2 ሚሊየን፣ በ2011 ዓ.ም 8.2 ሚሊየን እና በ2012 ዓ.ም 7.8 ሚሊዮን ሰዎች ላይ የኤችአይቪ ምርመራ የተደረገ ቢሆንም፤ በእነዚህ በሦስት ተከታታይ በጀት ዓመታት መገኘት የነበረው ከ1.2% በላይ ቢሆንም ማግኘት የተቻ ለው 0.8% (73,981)፣ 0.6% (51,093) እና 0.5% (41,070) ሰዎች ብቻ ኤችአ ይቪ በደማቸው የሚገኝ ሲሆን ይህም ከሚጠበቀው ከ50 መቶ በታች ሆኖ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ ምርመራዉ ተጋላጭ ተኮር አለመሆኑን ያሳያል፡፡

- ምንም እንኳን ሀገራችን የ2ኛውንና 3ኛው ዘጠና በአጠቃላይ ማህበረሰብ ክፍል ማሳካት የቻለች ቢሆንም በአፍላና ወጣት እንዲሁም ከ15 ዓመት በታች የሚገኙ ህጻናት ያለው አፈጻጸም ሲታይ በአፍላና ወጣት ወንዶች በተከታታይ 65% እና 81%፣ በሴቶች 74% እና 83% እንዲሁም በህጻናት 67% እና 74% በመሆን ዝቅተኛ ነው።

- የፀረ-ኤችአይቪ ሕክምናን አስመልክቶ በአዋቂዎች ላይ ከአስመዘገብነው የስኬት ጉዞ ጋር ሲነፃፀር የህፃናትና የአፍላ ወጣቶች ሕክምና በእጅጉ ወደኃላ ቀርቷል። ከ0-4 ዓመት ባሉ ህፃናት 26% ሲሆን፣ ከ5-10 ዓመት ባሉት ላይ 46% እና ከ10-14 ዓመት ባሉት ላይ 58% ነው። ከ15 ዓመት በታች በሚገኙ ህፃናት የቫይረሱን መጠን በሚፈለገው መጠን የማውረድ አፈፃፀምም 78.9% ብቻ ነው።

የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች፣ ህክምናቸውን እንዳያቋርጡ የድርሻዬን እወጣለሁ

- በሀገራዊ የኤችአይቪ ስርጭት ግምት በተመላከተው መሰረት (HIV Estimates & Projection Spectrum, 2019) ከተመዘገቡት አዲስ በኤችአይቪ ከሚያዙት 19% ያህሉ የተከሰቱት ከአራት ዓመት ዕድሜ በታች ባሉ ህፃናት ላይ ነው። ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን በጊዜው ምርመራ እንዲያገኙ በማድረግ ቫይረሱ በደማቸው የተገኘባቸውን ደግሞ ቶሎ የፀረ-ኤችአይቪ ሕክምና ላይ ማስቀመጥ የህፃናትን ሕይወት ከሞት ከመታደግ አንፃር ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ አስቸኳይና አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች ምክንያት ለህፃናት ወቅቱን የጠበቀ የኤችአይቪ ምርመራ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ትልቅ ዕንቅፋት ሲፈጥሩ ይስተዋላል። የፕሮግራም አፈጻጸም ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት በ2011 በጀት ዓመት 64% ጨቅላ ህጻናት ብቻ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ያደረጉ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት 52.9% ብቻ የፀረ-ኤችአይቪ መከላከያ መድኃኒት መውሰዳቸውን ለዚህ ማሳያ ይሆናሉ።

- ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተከታታይነት ያላቸዉ ፕሮግራሞች ቢተገበሩም በማህበረሰብ ደረጃ የሚተገበረዉ ስራዎች መቀዛቀዝ ዛሬም አፈጻጸሙ በሚፈለገው ደረጃ አልደረሰም። በ2012 በጀት ዓመት ኤችአይቪ በደማቸው ይገኛል ተብሎ ከሚጠበቀው 23,433 ነፍሰ ጡር እናቶች መካከል 76 ከመቶ ብቻ የጸረ-ኤችአይቪ መድኃኒት መውሰዳቸው፡

የፀረ-ኤችአይቪመድሃኒት ሳላቋርጥ በአግባቡ በመውሰዴ ጤናማና ደስተኛ ነኝ።

- የዓለም አቀፍ ወረረሽኝ የሆነው የኮሮና ቫይረስ በሽታ (ኮቪዲ-19) የአመራሩን፣ የጤናና ሌሎች ተቋማት ትኩረት አሟጦ በመውሰድ ለኤችአይቪ መከላከል የሚደረገውን እንቅስቃሴ የገታ ከመሆኑ በሻገር ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ላይ ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና እያሳደረ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በማህበረሰብና በጤና ስርዓት ላይ ባለው ጫና ይበልጥ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግ የተቀመጡ አገልግሎቶችን ለመስጠት አዳጋች እየሆነ ይገኛል፡፡

- የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽ ከወትሮ ይልቅ ስልታዊና ከፍተኛ አቅም የሚጠይቅ ሥራዎችን በመስራት ኤችአይቪ በደማቸው ይገኛል ተብሎ የሚጠበቁ ይበልጥ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን መለየትን ይፈልጋል፡፡ ይህም ከፍተኛ ሀብት የሚፈልግ ሲሆን ከውጭ የሚገኘው ሀብት እየቀነሰ መጥቶ ለግብዓት ማቅረቢያ ብቻ እየሆነ ይገኛል፡፡ ከአገር ውስጥ ሀብት የማሰባሰብ ሥራ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ በተደራጀና በህግ ማዕቀፍ እየተመራ አለመሆኑ፡፡

- ጊዜውንና ጥራቱን የጠበቀ ለተለያዩ የኤችአይቪ/ኤድስ ፕሮግራሞች ቀረፃ እንደ ግብዓትነት ሊውል የሚችል ስትራቴጂክ ኢንፎርሜሽን ማግኘት አለመቻልም ሌላኛው ተግዳሮት ሆኖ የቀጠለ ነው፡

## 4. የትኩረት አቅጣጫዎች

የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ-ብዙ ምላሽን ጨምሮ ዓለማቀፋዊ የጤና ምላሽ አሰጣጥን እንደሀገር የተገኙ ስኬቶችን በማጠናከር ያጋጠሙንን ተግዳሮቶች አዳዲስ አሰራሮችን በመዘርጋት በአዲስ መልክ መቃኘት ይኖርብናል፡፡ በመሆኑም እንደሀገር ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነትን በመጋራት በትብብር በመስራት ቀጥሎ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ነጥቦች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

**ሀ.የጤና ፕሮግራም ሙሉ ወጪን መሸፈን:** መንግስት ከዓለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የኤችአይቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ከክፍያ ነፃ በሆነ መልኩ እንዲሁም ሌሎች የጤና የአገልግሎቶችን በተመጣጠኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ በማድረስ ላይ ይገኛል፡፡ ነገርግን ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይገኝ የነበረው ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ የተለያዩ የሀገር ውስጥ ሀብት ማሰባሰቢያ መንገዶችን በማፈላለግ በዘርፉ የተመዘገቡትን አዎንታዊ ውጤቶች ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

**ለ.የጤና ስርዓትን ማጠናከር:** ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ውስጥ የተደረገው የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ኢንቨስትመንት የጤና ሥርዓትን ለማጠናከር ከፍተኛ እገዛ ያደረገ ሲሆን ይህም ለኮቪድ-19 ምላሽ እየጠቀመ ይገኛል፡፡ አሁንም የጤና ስርዓትን የማጠናከር ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠልና የጤና ባለሙያዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ተጨማሪ ሥራዎችን መስራት ይጠበቅብናል፡፡

**ሐ.የኤችአይቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ማረጋገጥ:-** የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት፣ የኤችአይቪ ምርመራ እና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የጤና አገልግሎቶችን ለሁሉም ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮችና የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

**መ. ሰብዓዊ መብትን መጠበቅ:-** እስካሁን የተገኘውን ሀገር አቀፍ የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ ምላሽ ዉጤት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ፕሮግራሞች የሰብዓዊ መብት መርህን መከተል አለባቸው፡፡ ይህ ማለት የኤችአይቪ አገልግሎቶች ለሁሉም ሰው ያለ ምንም መድሎና መገለል ተደራሽ መሆን ያለባቸው ሲሆን በተለይ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህብረሰብ ክፍሎችን ትኩረት በማድረግ ተደራሽ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ኤች አይቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ላይ የሚደርሰውን አድሎና መገለል ማቆም የሁላችንም ድርሻ ነው፡፡

**ሠ. የኤችአይቪ ፕሮግራሞች የሴቶችና የልጃገረዶችን መብትና የፆታ እኩልነት ያማከሉ እንዲሆኑ ማድረግ፡-** ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ሴቶች እና ልጃገረዶች ተሳትፎ እና ውሳኔ የመስጠት ሚና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በየደረጃው የሚቀረፁ የኤችአይቪ ፕሮግራሞች አሳታፊና ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

# በ2013 ዓ.ም የዓለም ኤድስ ቀን አከባበርን በተመለከተ ሴክተር መ/ቤቶች፣ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ሊያ ተኩሩባቸው የሚገቡ ዝግጅቶች

## I. ከዕለቱ በፊት የሚከናወኑ (Pre-WAD 2020 Activities)

- የ2020 መሪ ቃል "ኤችአይቪን ለመግታት፣ ዓለምአቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላ ፊነት" ሲሆን በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ «ዓለም አቀፍ ትብብር ፣ ኃላፊነትን መጋራት» በሚል የተተረጎመውን በሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲታወቅ ማድረግ፣

- ከመሪ ቃሉ ጋር በተያያዘ የአድቮኬሲና የሞቢላይዜሽን ሥራዎችን በአማራጭ መገናኛ ብዙሃን ማስተላለፍ፣

- በዓሉ በሚከበርበት ቦታ ከበዓሉ ቀን ቀደም ብሎ የጎዳና ላይ የሠርከስ ትርኢት ማሳየት እና የቅስቀሳ መልዕክቶችንም ማስተላለፍ፣

- በኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል፣ ህክምና፣ ድጋፍና እንክብካቤ ጉዳዮች በክልል/ ከተማ አስተዳደር፣ በዞን/ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ እንዲሁም በሴክተሮች በየደ ረጃው የፓናል ውይይት (በማህበረሰብ ላይ መስራትና ማሳተፍ፣ ምቹ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን መፍጠር፣ በበጉ ፈቃደኝነት እና በአርዓያነት መምራት ዙሪያ፣ እንዲሁም በወጣት ሴቶችና ይበልጥ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደረጉ) እንዲካሄድ ለክልሎች ማሳሰብና መከታተል፣

- ከመሪ ቃሉ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፖስተሮችና ባነሮች ማዘጋጀትና ማሰራጨት

- በዋዜማው ምሽት የሻማ ማብራት ሥነ-ሥረዓት እንዲኖር ማድረግ፣

- የፖሊስ የማርች ባንድ በታላላቅ ጎዳናዎች እየተንቀሳቀሱ ህብረተሰቡን እንዲቀ ሰቅሱ ማድረግ

## II. በዕለቱ የሚከናወኑ ተግባራት፣

- በአመራሮችና በሚመለከታቸው አጋር ድርጅቶች ወቅታዊ መልዕክቶች ይተላለ ፋሉ፣

- የጋራ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣ አቅጣጫውን ተከትሎ ውሳኔዎችን ማስተላ ለፍ፣

- በተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች፣ በባህላዊ ትርዒቶች፣ በሥነ-ጽሁፍ፣ ድራማና ፓናል ውይይት ማክበር፣

- የፖሊስ ማርች ባንድ በታላላቅ ጎዳናዎች በመንቀሳቀስ ህብረተሰቡን እንዲቀሰ ቅሱ ማድረግ፣

## III. ከበዓሉ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት (Post-WAD 2020 Activities)

- የዓለም ኤድስ ቀን አከባበር ሪፖርት ማጠናቀር፣
- ንቅናቄውን መሰረት በማድረግ የተጀመሩ ተግባራት ዓመቱን ሙሉ እንዲከናወኑ ክትትል ማድረግ፣
- በየደረጃዉ ያለውን ኤድስ ምክር ቤቶችንና ቦርድ ማጠናከር፣
- አፍላ ወጣቶችን ትኩረት ያደረጉ ፕሮግራሞችን ማጠናከር፣
- የመጀመሪያ 95 የሚያግዙ ስራዎችን ትኩረት መስጠት፣
- ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል ትኩረት መስጠት፣
- በተቋማት የሚተገበረዉን ሜይንስትሪሚንግ ማጠናከር፣
- ይበልጥ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ትኩረት ያደረገ የኤችአይቪ ፕሮግራ ሞችን ማጠናከር፣
- የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረቶችን ማቋቋምና ማጠናከር

በአጠቃላይ የዘንድሮውን የዓለም ኤድስ ቀን ስናከብር እስካሁን የነበረውን ሀገር አቀፍ የኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ዉጤቶችን ቀጣይነት ለማረጋገጥና ያጋጠሙ ትን ተግዳሮቶች ለምሳሌ የአመራር ትኩረት ማነስና በኮቪዲ-19 ጫና ዉስጥ መሆን፣ በማህበረሰቡ በተለይም በወጣቶች የሚታየውን ቸልተኝነት፣ በኤችአይቪ ቅድመ መከላከል ላይ የሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች፣ በአፍላና ወጣቶች እንዲሁም ህጻናት ላይ የሚታየውን የ3ቱ 90ዎች ዝቅተኛ አፈጻጸም፣ ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ እን ዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎትና የተጋላጭ ህጻናት ምርመራና የጸረ-ኤችአይቪ መከላከያ መድኃኒት ሽፋን ማነስ፣ ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝ ወገኞች እና ወላጆቻ ቸውን ላጡ ሕፃናት  በድጋፍና እንክብካቤ ሥራዎች ተደራሽ  እንዲሆኑ ማድረግ እና በተቋማት የሚተገበረውን የኤችአይቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ሥራዎችን ተቋማዊ ለማድረግ የላቀ አመራር በመስጠት እና እ.ኤ.አ በ2030 ኤድስን የማቆም ራዕይ ለማሳካት በጋራ የምንቆምበት ነው፡፡ በመሆኑም “ኤችአይቪን ለመግታት፣ ዓለምአቀፋዊ ትብብር ፣ የጋራ ኃላፊነት” እንሻለን፡፡



ራሴን እና ቤተሰቤን ከኤችአይቪና ከኮሮና ቫይረስ ለመከላከል ተገቢውን ጥንቃቄ አደርጋለሁ፡፡

በዓሉ በሚከበርበት ወቅት ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

UNAIDS

PEPFAR

UNFPA

AHF AIDS HEALTHCARE FOUNDATION

World Health Organization

unicef

project HOPE

psi Ethiopia

ORHA Ethiopia

dkt ETHIOPIA

NNPWE

ICAP Columbia University Mailman School of Public Health

fhi360 THE SCIENCE OF IMPROVING LIVES